# <u>መንግስት ህዝብና ሙዚቃ በኢትዮጵያ</u>

ዘነበ በቀለ

ለብዙ ዘመናት የኖረው የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነቱም ባህሉም ውበቱም ፍቅሩም ጠቡም ሲገለፅ የቆየው በኪነታዊ ጥበብ ነው። ሙዚቃም የበኩሉን ሲያወጣ ከመንግስታዊ ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆነ መልኩ አልነበረም። በዚህም ምክንያት ማህበረሰቡ በየአካባቢው ሲሰማ ያደገውን ዘፈንና በትምህርት ቤት የሚገኘውን መዝሙር ለይቶ የመረዳት ችግር ቢኖርበት አያስገርምም። በትምህርት የመተላለፊያው መንገድ የተዘጋ በመሆኑ እንዲሁ በልምድ በብዙዎች ዘንድ ሙዚቃ ማለት ዘፈን እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል። በዚህ ላይም መንግስታት የየራሳቸውን አገዛዝ ስልት ለማንፀባረቅ ስለሚጥሩ የሙዚቃ አሰራር ፈሊጥ መንገዱን እንዲስት ምክንያት ሆነዋል። መዝሙር በተለይ በተማሪዎችና በወታደሮች ዘንድ የሚዘወተር የአዘማመር ፈሊጥ ነው። መዝሙር በመልዕክቱም ሆነ በአሰራር ስልቱ ማህበራዊ ይሁን እንጂ! የመንግስታቱ ተፅዕኖ ያለበት ነው። መንግስታቱ በቀጥታ እጃቸውን አስገብተው ሳይሆን አንዳንድ እወደድ ባዮች በሚፈጥሩት አንጀባ የተነሳ ነው። በአፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት ይዘመሩ የነበሩት አብዛኞቹ መዝሙሮች በሳቸው ተክለ ሰውነት ዙሪያ በመሆኑ ከሳቸው ህልፈት በሁዋላ ለህፃናት የሚያገለግሉ አልሆነም።

"ይኑርልን ለክብራችን! - ሀይለስላሴ ድል አድራጊው ንጉሳችን"
“መንግስትን ለዳዊት ቡራኬን ለሴም — እንዳንት የተሰጠው ማንም ሰው የለም"
ወዘተ. ዛሬ ዘላቂ የህፃነት መዝሙሮች ሆነው ሊቀጥሉ አልቻሉም። ምክንያቱ ግልፅ ነው። ምክንያቱ ቀደም ሲል እንደተገፀው ይህ የሙዚቃ አይነት በጋራ በሚተረጎሙ ህዝባዊ ዕሴቶች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ነው። ስለዚህም የግላዊ እንጉርጉሮዎችን የጎሳዊ ዘፈኖችን ተመክሮ አይጋራም። መዝሙር በህዝብ ስሜት ውስጥ ዘልቆ የመግባትና ቅፅበታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ሀይልና አቅም አለው። ለምሳሌም ያህል ብንመለከት፦ በባህላዊው ቀረርቶና ፍከራ / ገረርሶ ሙዚቃ አማካኝነት ከፍተኛ መስዋዕት መከፈሉን ልብ ልንል ይገባል። በኛው ትውልድም ውስጥ ቢሆን በኢህአፓ የቀረበው አታጋይ መዝሙር፥

ቢፈለጥ አጥንቴ - ቢንቀረቀር ደሜ - ላዲስ ስርዓት ልምላሜ፣

የሚለው በርካታ ታጋዮችን ለትግል ያሰለፈና ለዓላማው በጀግንነትና በፅናት እንዲቆሙ ያደረገ ነው። በደርግ ጊዜም የህዝቡን ስሜት ስቦ የነበረው፥
"ተነሳ ተራመድ! ክንድህን አብርታ!
ላገር ብልፅግና ለወገን መከታ"

የሚለው መዝሙር ነበር። እዚህ ላይ ሊስተዋል የሚገባው ነገር አለ። በህብረ ብሄራዊነት ስር የሚደራጁት ሀይሎች ሁልጊዜ በጋራ ለሚያዘምራቸው ሃሳብ አፅእኖት የሚሰጡ ሲሆን ጠባብ ጎሰኞች ግን ህዝብን መኮርኮሪያ መሳሪያቸው የሚያደርጉት ጎሳዊና ባህላዊ ዘፈንን ነው። በዕርግጥ ዘፈን ከመዝሙር የበለጠ የማሰባሰብ ሀይል ያለው ነው የሚባልበትም ዘፈን ባካባቢ ቋንቋ ላይ መሰረት የአደረገ በመሆኑና በዚህ የሙዚቃ ስታይል ውስጥ ሁሉም ሰው መዝፈን ብቻ ሳይሆን እንደየአቅሙ የሚሳተፍበት ስፍራ ስለሚያገኝ ማለትም በጭብጨባ በድጋፍ ድምፅ በዕልልታ ወዘተ. መተባበር በመቻሉ በሌላ አነጋገር ዳር ዳሩን የሚያንጓብበውም ስለሚታቀፍ እንደ መዝሙር አፋጠ የተሳታፊውን ሁሉ ሙሉ ተሳትፎ የማይጠይቅ በመሆኑ ሊሆን ይችላል። ዘፈን መዝናኛ እንጂ ጠንከር ያለ መልዕክት ማስተላለፊያ ባለመሆኑ ከመዝሙር ይለያል በዚህም ለብዙ ተዋኸር አጀቢ ይስማማል።

ሌላው የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃ በፎርም በይዘት በስልት የተለያየ በመሆኑ ስርአቶቹን ባለመገንዘብ የተፈጠረ መፈላቀቅ አለ። ለምሳሌ፡ የማንጎራጎር የመዝፈን ድርሻ የሚሰጠው በዕድሜው የባለቀ ሰው እንጂ ለህፃናት አይደለም። ለህፃናት የሚፈቀደው መዝሙር ብቻ ነበር። ምክንያቱ እንጉርጉሮና ዘፈን ግጥሞቻቸው በተወሰነ ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ ባለመሆናቸው ባህላዊውን የዕድሜ ክልል ይጋፋሉና ነው። አንድ የአስር ዓመት ልጅ በእንጉርጉሮ ሰታይል በትዝታ ቅኝት፡

"የፍቅርሽ ትኩሳት እያንገበገበኝ — ሌሊትም አልተኛ ቀንም እንቅልፍ የለኝ"

ብሎ ቢዘፍን አሳዳጊ የበደለው መባሉ የማይቀር ነው። ለሴቷም ቢሆን የበለጠ ውግዘት ነው የሚደርስባት። ምክንያቱ ግልፅ ነው። ሴት ልጅ ውበታም ወይም ቆንጆ ከሚያሰኛት ነገር መሃል ውበቷን ድብቅ አርጋ መያዝ መቻሏ ነው። ፍቅሯን ባደባባይ የምታሳይ ሴት ምድቧ ሌላ ነው። ማንኛውም ሰው የተሰጠው የዕድሜ ክልል አለ። ሌላው ቀርቶ ለፖለቲካውም ጉዳይ ቢሆን ሃላፊነት በዕድሜ ዙሪያ የሚከፋፈል መሆኑን አባቶቻችን በጋዳ ስርአት ላይ አሳይተውናል። ያ ሲሆን ደግሞ የመተካካትና የመማማር ሂደቶች እውን ይሆናሉ። ወላጅ ተቀምጦ የጎረቤትን ባልና ሚስት የጎረቤት ልጅ ላስታርቅ ብሎ አይጨነቅም። በብዙ ምክንያቶች ለሱ ከዕድሜው ክልል ውጭ የሆነ ጉዳይ ስለሚሆን። ሙዚቃውም ይህን ሁሉ ህዝባዊ ጠባይ ያቀፈ ነው።

በዘመናዊ ሙዚቃ አሰራሮች ውስጥ ይህ ገደብ በወጣቱ የተጣሰ መሆኑ አያጠያይቅም። ትንሽ ከህንድ ትንሽ ከሱዳን ትንሽ ከአሜሪካ ትንሽ ከተለያዩ ጎሳዎች ባህል ለጣጥፎ አዲስ ሙዚቃ የሚያደርገው የሙያ ሰው የሙያው ተጠሪና ተቆርቋሪ ነኝ ሊለን ከቶውንም አይቻለውም። ቀደም ሲል የባህል ሞዛይክ እየተባለች የምትጠራው ኢትዮጵያ፣ ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ የበርካታ ጎሳዎች ልዩ

ባህል እደሚጠፋ መጠራጠር አይቻልም። እንደ ቀድሞው አንድ ስልት ተመሳሳይ ፎርምና ስታይል ያለው የኢትዮጵያ ሙዚቃም አይኖርም። ምክንያቱ አሰራሩ ከባህሉ ያፈነገጠ በመሆኑ ነው። አንዳንድ የኢዶል ፕሮግራምን አቀራረብ ከፈረሱ የቀደመ ጋሪ አድርገን ብንመለከት ስህተት አይሆንም። የህፃናትን በዘፈን ውድድር የመሳተፍ ሁኔታ አጥብቆ ማወገዝ የዜግነት ግዴታ ነው። ይህ ምናልባት የአብዮታዊ ዲሞክራሲን የባህል ለውጥ ለማስፈፀም የሚጥሩበት ፕሮግራም ሊሆን ይችላል። ያም ቢሆን ከፖለቲካው ጋር የሚቀራኝ እንጂ ከባህላዊውም ሆነ ዘመናዊ የኪነጥበብ ዕድገት ጋር የሚታይ አይሆንም። የኪነትን ዕድገት በተዛባ መልኩ ለማንፀባረቅ የአጫፋሪነት ባህርይ ይዘው የሚልከሰከሱ የሙያው ሰዎች ትዝብቱን ከህዝብ ብቻ ሳይሆን ከመሪዎችም ማግኘታቸው እየታየ ነው።

የአቶ መለስ የኪነት ሰዎችን ጋብዞ ማሳሰቢያ የመስጠቱ ጉዳይ የሚያመለክተው ይኽንኑ ነው። አቶ መለስ ከሳቸው በፊት የኖሩትንም ሆነ አሁን ያሉትን አምባገነኖች ጠባይና ውድቀት ጠንቅቀው ስለሚያውቁት ጊዜያዊ የጥቅም ሰዎችና አድርባዮች እንደፈለጉት ቢልሞጠሞጡ አያደንቋቸውም።
የቀኑ ጊዜ መዝሙሩም ሆነ ዘፈኑ ከህዝብ ቁጣ የሚሰውር አለመሆኑን በስርዐት የሚረዱ ናቸው። በኪነጥበብ ስም ሊሸቅል የተዘጋጀው ወይም ሽቀላውን ያጧጧፈው ለማን ሲል እንደሚቀላምድ ይረዱታል። አቶ መለስ ይህንን አይነቱ እንኳ አይጠፋቸውም። በዚህ አይታሙም። የሚታማው ሙያውን ለሆዱ፤ ለክብሩ፤ ለዝናው ሲል የሸጠው ከያኒ ነኝ ባይ ነው።

ይህ ደግሞ ይዋል ይደር እንጂ በህዝብ ያስጠይቃል። ኪነጥበብ የህዝብ ንብረት ነች። ህዝቡ በርሃብ ሲሰቃይ ስንቱ የኪነጥበብ ሰው ነው በኢትዮጵያ ሙዚቃ ላይ ሸቅሎ ያተረፈው? ስንቱ ነው የህዝቡን ችግር ችግሬ ብሎ፣ ልሳኑ ሆኖ ያስተጋባለት? ስንቱ ነው መብቱ ለተረገጠው ከቦታ ቦታ እየተንከራተተ ለሚሰቃየው የቆመው? በዚያ ኮንሰርት ቀርቦበታል? ከቆሻሻ መጣያ ላይ ምግቡን የሚያገኘው ህፃን በፊልም ተቀርፆ የዐለም ህዝብ እጁን እንዲዘረጋ ቀስቅሶለታል? ከያኒው ጋዜጠኛው የሚያደርገውን ያህል እንኳ ለህዝቡ መብት ያደረገው ትግል ምንድነው? አዲስ ካሴት ለኪስ ወይስ ለመለስ? በየትኛው ጉዳይ ላይ ነው ኪነ ጠበብ ህዝባዊነቷን እንድታሳይ የሆነው? ስለዚህም አቶ መለስ ስለቀለበት መንገድ፣ ስለ ግቤ ግልገል፣ ስለ አባይ ግድብ፣ ስለተከዜ፤ የሚያላዝኑ ሰዎችን ሲመለከቱ የፓርቲያቸውን አባላት እንዳሉት ሁሉ ወራዶች ናችሁ ቢሉዋቸው "ዶሮን ሲያታልሏት ….. " እያሉ ብዙ ጊዜ የሚጠቅሱትን ጥቅስ ምንነት የገባቸው መሆኑን ይመሰክራል እንጂ! አቶ መለስን ከርፋፋ ጅል አያስብልም።

የኪነ ጥበብ ሰው ተግባሩን ከረሳ፣ ማንነቱን ካዋረደ መጠራጠራቸውና ሰብስበው መገሰፃቸው ተገቢ ነው የሚሆነው። የሀብቱ ምንጭ የሆነውን የኢትዮጵያን ህዝብ ከድቶ የሚቆም ከያኒ፣ ለኔ ይበጀኛል አለማለታቸው "የፊት ወዳጅክን በምን ቀበርከው በሻሽ የሁዋለኛው እንዳይሸሽ" የሚለውን አስታውሷቸው ነውና ትክክል

ነው። ምክንያቱም ኪነጥበብም ሆነች ሀቀኛ የሙያው ሰዎች ህዝብን ክድተው ህዝብን በሚያሰቃይ ተግባር ላይ ለሚሰማሩ መንግስታት ገባሪ ሆነው የታዩበት ዘመን የለምና። ካሉ እነኛ ተራ በሙያው ላይ ለመነገድ የቀረቡ እንጂ የህዝብ አጋርም ሆነ የሙያው ሰዎች የሚያደርጋቸው አንዳችም ሀቅ የለ።
አቶ መለስም ሆኑ የወያኔ ጀሌአቸው፣

- የህዝብ ያልተመጣጠነ ኑሮ ምንጭ የሆነውን ዘረፋ እየፈፀመ
- አዛውንት ከመንገድ ወድቀው የሚለምኑ መሆናቸው ሳይቀር
- የሀገሪቱ ገበሬ ከመሬቱ እየተፈናቀለ የሚባረርበት ስርአት እያለ
- የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች እንዲከስሙና ያሉትም ሀብታቸውን ወደውጭ እንዲያሸሹ የሚገፋፋ ሁኔታ እየተፈጠረ
- ቤተሰብ እራሱን ማስተዳደር አቅቶት በፈረቃ እንዲበላ ሲሆን
- መብራት ውሃ የህልም ሽታ ሆነው እያለ
- አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ ከመደብር ሲጠፉ እየተስተዋለ
- የሀገር መሬት ለውጭ ዜጋ ሲቸበቸብ እያየ
- ስርአቱ ባፍ ኢትዮጵያዊነት በተግባር ጠባብ ጎሰኝነትን እያራመደ
- ባጠቃላይ ጠባብነት እንደ ርዕዮተ አለም እየተስተናገደ

ባለበት በዚህ ወቅት ስቃይና መከራ በነዋሪው ህዝብ ላይ ሲፈፀም እያየ ንሰብሆ የሚል ከያኒ እኔ አይቼም አላውቅና የእናንተን ሁኔታ አላምነውም፣ እጠራጠራለሁ ማለታቸው ተገቢ ስጋት ነው። አዎ! እውነተኞቹ የሙያው ሰዎች ጥበብን በገንዘብ እንደማይለውጡ ተረድተዋልና። አዎ! መሬት ላራሹ የሚለው መፈክር በገበሬው መቃብር ላይ ሲደመደም ቆሞ የሚመለከት ኢትዮጵያዊ አለመኖሩን አውቀዋልና። ስለዚህም ያቶ መለስ አላምናችሁም ስጋት ተገቢ ነው። ለእበላ ባይ የኪነት ሰዎች በአውቶቢስ ተጭኖ ሄዶ ጀግንነትን መጠበቅ አይቻልም የሚል! መልዕክት ስላለው አንድም ከዚህ በላይ ሆኖ መታየት አለበለዚያም በሚጠበቁበት መዋል አማራጫቸው ይሆናል። ኪነጥበብም ሆነ ህዝብ በሀቀኛ ልጆቻቸው መስዋዕትነት ይከበራሉ!!

ኢትዮጵያ ለዘለአለም ትኑር!!